የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፮
አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25[th] Year No.76
ADDIS ABABA 7[th] August,2019

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፯/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ………………………………ገጽ ፲፩ሺ፫፻፹

**Content**

Proclamation No. 1147/2019

Movable Property Security Right Proclamation ……………………………………Page 11380

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፯/፪ሺ፲፩

## በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ

ዋስትናው የተጠበቀ ዘመናዊ የብድር ሥርዓት እንዲኖር እና ግለሰቦችና ተቋማት ተንቀሳቃሽ ንብረታቸውን በማስያዝ ሥራ ላይ የሚውል አዲስ ካፒታል ማግኘት እንዲችሉ፣ በሂደትም በየደረጃው ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የፋይናንስ ተደራሽነትንና ተጠቃሚነትን ለማስፋፋት፣ በዋናነት በከተሞች ላይ ብቻ ውስን ሆኖ የቆየውን የባንክ አገልግሎትና ተደራሽነት ወደ ገጠሩ ማህበረሰብ ለማስፋፋትና ለማሳደግ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል በመሆኑ፤

ተንቀሳቃሽ ንብረትን በዋስትና አስይዞ ብድር ማግኘት የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋትና የማስፈጸሚያ መንገዱንም ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

ለዋስትና በተያዘ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በተወዳዳሪ ባለመብቶች የሚነሳ የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን የሚያስችል አንድ ወጥና ሁሉን አቀፍ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩)መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

## PROCLAMATION No. 1147/2019

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR MOVABLE PROPERTY SECURITY RIGHT

**WHEREAS,** modern secured transactions system enables individuals and entities to use their movable assets as security for credit generating new productive capital, expands investments, creates more job opportunity, increases production and productivity, fosters access to and usage of financial products and services, creates opportunity to expand banking services to rural areas;

**WHEREAS,** it is necessary to provide for the creation of security right in movable property, ensure their publicity and effectiveness through efficient enforcement mechanisms;

**WHEREAS,** establishing single comprehensive electronic registration regime for secured transactions in movable property to determine priority right among competing claimants is necessary;

**NOW, THEREFOR,** in accordance with Article 55(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 52.70

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G P.O.Box 80001

፫/ የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የመረጃ ፍለጋ ጥያቄ ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የመያዣ መዝገቡ ምክንያቱን ለአስመዝጋቢው ወይም ለመረጃ ፈላጊው ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

**፳፮. <u>የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ምርመራ እንዳያደርግ ስለመከልከሉ</u>**

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የማስታወቂያ ምዝገባ ወይም የፍለጋ ጥያቄ ወይም የማስታወቂያ ይዘትን መመርመር አይችልም፡፡

**፳፯. <u>ለመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚያስፈልጉ መረጃዎች</u>**

፩/ የመጀመሪያ ማስታወቂያ የሚከተሉትን አግባብነት ባላቸው ቦታዎች የተሞሉ መረጃዎችን መያዝ ይኖርበታል:-

ሀ) በአንቀጽ ፳፰ መሠረት የመያዣ ሰጪውን መለያ ቁጥር እና ሙሉ ስም፣

ለ) በአንቀጽ ፳፱ መሠረት ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ ወይም የተወካዩን መለያ፣

ሐ) የመያዣ ሰጪውን እና ዋስትና ያለውን ገንዘብ ጠያቂ አድራሻ፣

መ) በአንቀጽ ፴ መሠረት መያዣውን የሚያብራራ መግለጫ፣

ሠ) ምዝገባው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ እና

ረ) ለስታትስቲካዊ ዓላማ ብቻ እንዲሰበሰብ በመመሪያ የሚወሰን ማንኛውም ሌላ መረጃ፡፡

፪/ ከአንድ በላይ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በሚኖርበት ጊዜ መረጃዎች ለእያንዳንዱ መያዣ ሰጪ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በተናጠል መሞላት ይኖርባቸዋል፡፡

**፳፰. <u>የመያዣ ሰጪው መለያ</u>**

፩/ መያዣ ሰጪው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ:-

ሀ) መለያው በመመሪያ የሚወሰን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር፣ እና



3/ If the registration of a notice or a search request is rejected, the Collateral Registry shall communicate the reason to the registrant or searcher without delay.

**26. <u>No Verification by the Collateral Registry Office</u>**

The Collateral Registry Office may not conduct any scrutiny of the content of a notice or search request.

**27. <u>Information Required in an Initial Notice</u>**

1/ An initial notice shall contain the following information in the relevant designated field:

a) the identifier and name of the grantor in accordance with Article 28;

b) the identifier of the secured creditor or its representative in accordance with Article 29;

c) an address of the grantor and the secured creditor;

d) a description of the collateral in accordance with Article 30;

e) the period of effectiveness of the registration; and

f) any other information to be prescribed in the directive collected for statistical purpose only.

2/ If there is more than one grantor or secured creditor, the required information shall be entered separately for each grantor or secured creditor.

**28. <u>Grantor Identifier</u>**

1/ Where the grantor is a natural person:

a) the grantor identifier is the unique identification number as prescribed in the directive; an

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከመያዣ ሰጪው በጽሑፍ በደረሰው ጥያቄ መሠረት በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ካልፈፀመ መያዣ ሰጪው የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያው በመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በኩል እንዲመዘገብ መጠየቅ ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚጠየቅን የማሻሻያ ወይም የስረዛ ማስታወቂያ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ መዝግቦ ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ግልባጭ የሚደረግ ተገቢ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

፴፯. <u>የመፈለጊያ መስፈረት</u>

ለሕዝብ ክፍት በሆነው የመያዣ መዝገብ ውስጥ ያለን መረጃ:-

፩/ የመያዣ ሰጪውን መለያ፣ ወይም

፪/ የመያዣን መለያ ቁጥር፣

በመጠቀም መፈለግ ይችላል፡፡

፴፰. <u>ስለፍለጋ ውጤት</u>

፩/ በዚህ ክፍል የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ የፍለጋ ጥያቄ ሲቀርብ የመያዣ ምዝገባ ሥርዓቱ ወዲያውኑ:-

ሀ) ፍለጋው የተከናወነበትን ቀን እና ሰዓት፣

ለ) እያንዳንዱ ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ፣ ወይም

ሐ) ከፍለጋው መሥፈርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰል መረጃ አለመገኘቱን፣

የሚያሳይ ምላሽ ይሰጣል፡፡

፪/ ተቃራኒ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ በመያዣ መዝገቡ ለፍለጋ ጥያቄ የተሰጠ ማስረጃ ስለ ፍለጋው ይዘት ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

5/ If the secured creditor does not comply with the grantor's written request referred to in Sub Article (4) of this Article within ten working days after its receipt, the grantor is entitled to seek the registration of an amendment or cancellation notice through the Collateral Registry Office.

6/ An amendment or cancellation notice in accordance with Sub Article (5) of this Article shall be registered by the Collateral Registry Office without delay upon the issuance of the relevant order with a copy of the order to the secured creditor.

37. <u>Search Criteria</u>

A public search of a record may be conducted according to:

1/ the identifier of the grantor; or

2/ the serial number of the collateral.

38. <u>Search Results</u>

1/ Upon submission of a search request that satisfies the requirements of this Part, the Collateral Registry shall, without delay, provide a search result that

a) indicates the date and time when the search was performed;

b) sets forth all information in each registered notice that contains information matching the search criterion exactly; or

c) indicates that no registered notice contains information matching the search criterion exactly.

2/ A search result issued by the Collateral Registry is proof of its contents in the absence of evidence to the contrary.

፪/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በመዝገቡ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ጠብቆ የማቆየት እና መረጃው ሲጠፋ ወይም ሲጐዳ መልሶ የማደራጀት ግዴታ አለበት፡፡

፵፫. <u>መረጃን ከመያዣ መዝገብ እና ከማህደር ስለማስወገድ</u>

፩/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት በሆነው የምዝገባ ማስታወቂያ ውስጥ ያለን መረጃ የማስታወቂያው ምዝገባ የተፈፃሚነት ጊዜ ሲያበቃ ማውጣት አለበት፡፡

፪/ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ለሕዝብ ክፍት ከሆነው መዝገብ የተወገደ መረጃን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ መሠረት መልሶ ሊገኝ በሚያስችል መልኩ ለአሥር ዓመት ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

፵፬. <u>የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የተጠያቂነት ወሰን</u>

የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት በሌሎች ሕጎች ተጠያቂነት የሚኖረው:-

፩/ ለመረጃ ፈላጊው የተሰጠ ምላሽ ወይም ለመዝጋቢው ተሰጥቶ በተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ውስጥ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማካተት፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ (፭) እና (፮) መሠረት በዋስትና መዝገብ ውስጥ መረጃ ሲመዘገብ ስህተት በመፈፀም ወይም መረጃ ባለማስገባት ወይም ከመዝገቡ ውስጥ በስህተት መረጃ በማውጣት፤

፫/ የመያዣ መዝገቡ ለመዝጋቢው የተመዘገበ ማስታወቂያ ግልባጭ ባለመስጠቱ፤ ወይም

2/ The Collateral Registry Office shall preserve information contained in its records and reconstruct it in the event of loss or damage.

43. <u>Removal of Information from the Collateral Registry and Archival</u>

1/ The Collateral Registry Office shall remove information in a registered notice from its public records only upon the expiry of the period of effectiveness of the registration of a notice.

2/ The Collateral Registry Office shall archive information removed from its public records for ten years in a manner that enables the information to be retrieved by the Collateral Registry in accordance with Article 37.

44. <u>Limitation of Liability of the Collateral Registry Office</u>

Any liability that the Collateral Registry Office may have under other laws is limited for loss or damage caused by:

1/ an error or omission in a search result issued to a searcher or in a copy of a registered notice provided to the registrant;

2/ In accordance with Article 36 (5) and (6) an error or omission in entering or failing to enter information in the records or in erroneously removing information from the records;

3/ a failure of the Collateral Registry to send a copy of the registered notice to the registrant; or

**፵፰. <u>የዋስትና መብት መኖሩን ማወቅ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ</u>**

ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዋስትና መብት መኖሩን ማወቁ በዚህ አዋጅ መሠረት ያለውን የቀዳሚነት መብት አያሳጣውም፡፡

**፵፱. <u>በሶስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የዋስትና መንገድ በሚለወጥበት ጊዜ ስለሚኖሩ ተወዳዳሪ የዋስትና መብቶች</u>**

በዚህ ክፍል ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የነበረ የዋስትና መብት የተመሠረተበት መንገድ ሲለወጥ የጊዜ ክፍተት እስከሌለው ድረስ የቀዳሚነት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

**፶. <u>ታሳቢ ብድር እና ታሳቢ መያዣ</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፭ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀዳሚ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላ የተገቡ ግዴታዎችን ጨምሮ ሁሉንም ዋስትናቸው የተጠበቁ ግዴታዎችን ይሸፍናል፡፡

፪/ ከምዝገባው በፊት ወይም በኋላ በመያዣ ሰጪው የተገኘ ወይም የተፈጠረ ቢሆንም ቀዳሚ የዋስትና መብት በመያዣ መዝገቡ በማስታወቂያ ተለይተው የተመዘገቡ ዋስትናዎችን በሙሉ ይሸፍናል፡፡

**፶፩. <u>በተያያዥ ገቢ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት</u>**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ የሆነ የተያያዥ ገቢ ዋስትና መብት ከተወዳዳሪ የዋስትና መብት ይልቅ የገቢው ምንጭ በሆነው ዋስትና ላይ በተመሠረተው የቀዳሚነት መብት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**48. <u>Irrelevance of Knowledge of the Existence of a Security Right</u>**

Knowledge of the existence of a security right on the part of a secured creditor does not affect its priority under this Proclamation.

**49. <u>Competing Security Rights in the Case of a Change in the Method of Third-Party Effectiveness</u>**

Unless otherwise provided in this Part, the priority of a security right is not affected by a change in the method by which it is made effective against third parties, provided there is no time gap during which the security right is not effective against third parties.

**50. <u>Future Advances and Future Collateral</u>**

1/ Subject to Article 55, the priority of a security right extends to all secured obligations, including obligations incurred after the security right became effective against third parties.

2/ The priority of a security right covers all collateral described in a notice registered in the Collateral Registry, whether they are acquired by the grantor or come into existence before or after the time of registration.

**51. <u>Priority of a Security Right in Proceeds</u>**

Subject to Article 58, a security right in proceeds that is effective against third parties under Article 14 has the same priority over a competing security right as the security right in the collateral from which the proceeds arose.

**፶፪. በውህድ ወይም በምርት ውስጥ የተቀላቀሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት**

፩/ የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብት ከዋሉ ዕቃዎቹ ከመቀላቀላቸው በፊት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነው የዋስትና መብት ዕቃዎቹ ከተቀላቀሉ በኋላ ከሚመሰረት የዋስትና መብት በፊት የቀዳሚነት መብት አለው፡፡

፪/ የተቀላቀሉ ወይም የተዋሃዱ ዕቃዎች ከአንድ ለሚበልጥ የዋስትና መብቶች ከዋሉና በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆኑ የመብቶቹ ቀዳሚነትና ዋጋ ዕቃዎቹ በተዋሃዱበት ጊዜ ባለው መሠረት ይሆናል፡፡

**፶፫. በማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ ላይ ስለሚኖር ቀዳሚ የዋስትና መብት**

፩/ የዋስትና መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ በሆኑ ወይም ሊሆኑ በሚችሉ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ሊመሠረት ወይም ሊቀጥል ይችላል፡፡ ሆኖም መብቱ በመደበኛ የግንባታ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተጓዳኝ የዋስትና መብት በሌሎች ህጎች ከተመሠረቱና ተፈፃሚ ከሆኑ ተወዳዳሪ መብቶች ይልቅ የቀዳሚነት መብት አለው፡፡

**፶፬. መያዣውን የገዛ፣ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም እንዲጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ሰው መብቶች**

፩/ የዋስትና መብት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ሆኖ እያለ መያዣው በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ ከተላለፈ፣ ከተከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከተሰጠ ገዢው ወይም መብቱ የተላለፈለት፣ የተከራየ ወይም የተፈቀደለት በዚህ አንቀጽ እንደተደነገገው ካልሆነ በስተቀር የንብረቱ ባለመብት የሚሆነው በላዩ ላይ ያለው የዋስትና መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ነው፡፡

**52. Priority of Security Right in Corporeal Assets Commingled in a Mass or Product**

1/ If more than one security right extends to commingled goods, a security right that is effective against third parties before the goods become commingled has priority over a security right that is not effective against third parties at the time the collateral becomes commingled goods.

2/ If more than one security right in commingled goods is effective against third parties, the security rights rank equally in proportion to the value of the collateral at the time it became commingled goods.

**53. Priority of Security Right in Accessories to Immovable**

1/ A security right may be created in corporeal assets that are accessories to immovable or may continue in corporeal assets that become accessories to immovable. A security right, however, may not be created in ordinary building materials incorporated into an immovable.

2/ A security right made effective against third parties in an accessory to immovable under this Proclamation has priority over a competing right created and made effective against third parties under other applicable laws.

**54. Rights of Buyers or Other Transferees, Lessees or Licensees of Collateral**

1/ If the collateral is sold or otherwise transferred, leased or licensed while the security right in that asset is effective against third parties, the buyer or other transferee, lessee or licensee acquires its right subject to the security right except as provided in this Article.

፫/ በመደበኛ የንግድ ሥራ ሂደት ለሚቀርቡ የአገልግሎት ወይም የአቅርቦት ክፍያን ወይም አፈጻጸምን ለማረጋገጥ ዕቃዎችን ለዋስትና በይዞታ ሥር ለማቆየት የሚያስችል የዋስትና መብት እስካለ ድረስ ይህ የይዞታ መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፶፮. ከተገኘ የዋስትና መብት ጋር የሚወዳደር ሌላ የዋስትና መብት

፩/ በፍጆታ ዕቃዎች፣ በመሣሪያዎች እና በአዕምሯዊ ንብረቶች ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው፦

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ንብረቱን በይዞታው ሥር ካደረገ፣ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ባደረገ ወይም አዕምሯዊው ንብረት ላይ መብት ባገኘ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ እንደሆነ፣

ነው፡፡

፪/ በንግድ ዕቃ ላይ የተገኘ የዋስትና መብት መያዣ ሰጪው ከመሠረተው ሌላ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ቀዳሚነት የሚኖረው፦

ሀ) የተገኘ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን በይዞታው ሥር ካደረገ፣ ወይም

ለ) መያዣ ሰጪው ሀብቱን በይዞታው ሥር ከማድረጉ ቀደም ብሎ የተገኘ የዋስትና መብት ማስታወቂያ የተመዘገበ ከሆነ፣ እና

3/ A possessory lien on goods which secures payment or performance of an obligation for services or materials furnished with respect to goods by a person in the ordinary course of the person's business has priority over a security right in the goods as long as the holder of the possessory lien remains in possession of the goods.

## 56. Acquisition Security Right Competing with Non-Acquisition Security Right

1/ An acquisition security right in consumer goods, equipment, or intellectual property has priority as against a competing non-acquisition security right created by the grantor provided that:

a) the acquisition secured creditor is in possession of the asset; or

b) a notice with respect to the acquisition security right is registered in the Collateral Registry within seven working days after the grantor obtains possession of the asset or acquires a right in intellectual property.

2/ An acquisition security right in inventory has priority as against a competing non-acquisition security right created by the grantor if:

a) the acquisition secured creditor is in possession of the asset; or

b) a notice with respect to the acquisition security right is registered in the Collateral Registry before the grantor obtains possession of the asset; and

፪/ በዋስትና የተያዘ ተላላፊ ሰነድ የተላለፈለት ሰው ሰነዱን ተቀብሎ በይዞታው ሥር ካደረገ፣ የንብረት ሽያጩ ወይም ዝውውሩ ሌላ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መብትን እንደሚጎዳ ባለማወቅ ዋጋ ከፍሎበት ከሆነ፣ መብቱ በሰነዱ ወይም በሰነዱ በተሸፈኑ ግዑዝ ሀብቶች ላይ ካለ እና በዚህ አዋጅ መሠረት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ነፃ ሆኖ ያገኛል፡፡

፷፭. ሴኩሪቲዎች

፩/ በሰነድ የተደገፉ ሴኩሪቲዎችን በይዞታው ሥር በማድረግ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ያደረገ የዋስትና መያዣ መብት፣ መያዣ ሰጪው በሴኩሪቲዎች ላይ ከፈጠረውና ማስታወቂያ ለማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ካደረገው ሌላ ተፎካካሪ የዋስትና መብት ቀደምትነት ይኖረዋል፡፡

፪/ በአውጪው ወይም እርሱን በመወከል በኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች ላይ ስለዋስትና መያዣ መብት በተዘጋጀ መዝገብ ላይ መግለጫ በመጻፍ ወይም ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን ስም እንደባለመብት መመዝገብ በሴኩሪቲዎቹ ላይ በሌላ ማንኛውም መንገድ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ በምዝገባው የተገኘው መብት ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

፫/ የቁጥጥር ስምምነት በመፈራረም በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ የሆነ የኤሌክትሮኒክ ሴኩሪቲዎች የዋስትና መብት በእነዚሁ ሴኩሪቲዎች ላይ ማስታወቂያ በማስመዝገብ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ ከሆነው የዋስትና መብት ይልቅ ቀዳሚነት ይኖረዋል፡፡

2/ A transferee of an encumbered negotiable document that obtains possession of the document and gives value without knowledge that the sale or other transfer is in violation of the right of the secured creditor under the security agreement, acquires its right free of a security right in the document and the corporeal assets covered thereby that is made effective against third parties under this Proclamation.

65. Securities

1/ A security right in certificated securities made effective against third parties by the secured creditor's possession of the certificate has priority over a competing security right created by the same grantor in the same securities made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry.

2/ A security right in electronic securities made effective against third parties by a notation of the security right or registration of the name of the secured creditor as the holder of the securities in the books maintained for that purpose by or on behalf of the issuer has priority over a security right in the same securities made effective against third parties by any other method.

3/ A security right in electronic securities made effective against third parties by the conclusion of a control agreement has priority over a security right in the same securities made effective against third parties by registration of a notice in the Collateral Registry.

**፸. የተሰብሳቢ ሂሳብ ባለዕዳ ስለሚደረግለት ጥበቃ**

በዚህ አዋጅ በተቃራኒው ካልተደነገገ በስተቀር በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት መመሥረት ለሂሳቡ መነሻ በሆነው ዋናው ውል የተካተቱ የክፍያ ሁኔታዎችን ጨምሮ የባለዕዳውን መብትና ግዴታ ከእርሱ ፈቃድ ውጭ አያውክም፡፡

**፸፩. በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብትንና ክፍያን ስለማሳወቅ**

፩/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የዋስትና መብት ተፈፃሚነት የሚኖረው ባለዕዳው በዋስትና የተያዘውን ተሰብሳቢ ሂሳብና ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂን በሚገባ የለየ ማስታወቂያ ሲደርሰው ነው፡፡

፪/ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የተመሠረተ የዋስትና መብት ከማስታወቂያ በኋላ የሚፈጠር ተሰብሳቢ ሂሳብንም ሊያካትት ይችላል፡፡

፫/ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ ስለተመሰረተው የዋስትና መብት ማስታወቂያ እስከሚደርሰው ድረስ በዋናው ውል መሠረት የክፍያ ግዴታውን ይፈፅማል፡፡ ባለዕዳው ማስታወቂያው ከደረሰው በኋላ ከግዴታው ነፃ የሚሆነው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ክፍያን በመፈፀም ወይም በማስታወቂያው ወይም በገንዘብ ጠያቂው በጽሑፍ ተቃራኒ ማሳወቂያ ከተሰጠው ብቻ ነው፡፡

፬/ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ባለዕዳ በተሰብሳቢ ሂሳቡ ላይ ስለተመሰረተና ከአንድ በላይ የሆነ የዋስትና መብት ማስታወቂያ ከመያዣ ሰጪው ከደረሰው መጀመሪያ በደረሰው ማስታወቂያ መሠረት ክፍያ በመፈፀም ከግዴታው ነፃ ይሆናል፡፡

**70. Protection of the Debtor of the Receivable**

Except as otherwise provided in this Proclamation, the creation of a security right in a receivable does not affect the right and obligation of the debtor of the receivable, including the payment terms contained in the contract giving rise to the receivable, without its consent.

**71. Notification of a Security Right and Payment of a Receivable**

1/ Notification of a security right in a receivable is effective when received by the debtor of the receivable if it reasonably identifies the encumbered receivable and the secured creditor.

2/ Notification of a security right in a receivable may relate to receivables arising after notification.

3/ Until the debtor of the receivable receives notification of a security right in a receivable, it is discharged by paying in accordance with the original contract. After the debtor of the receivable receives notification of a security right in a receivable, it is discharged only by paying the secured creditor or, if otherwise instructed in the notification or subsequently by the secured creditor in a writing received by the debtor of the receivable.

4/ If the debtor of the receivable receives notification of more than one security right in the same receivable created by the same grantor, it is discharged by paying in accordance with the first notification received.

፪/ መያዣ ሰጪው ወይም መያዣውን በይዞታው ሥር ያደረገ ማንኛውም ሌላ ሰው መያዣውን ዋስትና ላለው ገንዘብ ጠያቂ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ የመያዣ ምዝገባ ጽሕፈት ቤት የፖሊስ ኃይል ርክክቡን እንዲያስፈጽም የማዘዝ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ሳይወስድ በመያዣ ሰጪው ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳለ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ለማድረግ ወይም ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

## ፹፪. ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ለማስተላለፍ ስላለው መብት

፩/ ግዴታ አለመፈጸምን ተከትሎ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ባለበት ሁኔታ ወይም ከንግድ አሠራር አንፃር ተገቢ የሆነ ዝግጅት ወይም ማሻሻያ በማድረግ ለመሸጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት ይችላል፡፡

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣው የሚሸጥበት፣ የሚተላለፍበት፣ የሚከራይበት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የሚሰጥበትን መንገድ፣ ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታና ሌሎች ሁኔታዎች ማመቻቸት ይችላል፡፡ ይህም መያዣውን በተናጠል፣ በከፊል ወይም በጠቅላላ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማከራየት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ የመስጠት ምርጫን ይጨምራል፡፡

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የመያዣውን ባለቤትነት በሐራጅ ለገዛው ሰው ማስተላለፍ፣ ወይም በሁለተኛው ሐራጅ ገዢ ካልቀረበ በመጀመሪያው ሐራጅ በተወሰነው የመነሻ ዋጋ መያዣውን የመውሰድና ባለቤትነቱም እንዲተላለፍለት ማድረግ ይችላል፡፡

2/ If the grantor or any other person in possession of the collateral objects to give possession to the secured creditor the Collateral Registry Office shall have the power and duty to order the police force to execute possession.

3/ The secured creditor may, without removal, render the collateral unusable and dispose of it on the grantor's premises.

## 82. Right of the Secured Creditor to Dispose of the Collateral

1/ After default, the secured creditor is entitled to sell or otherwise dispose of lease or license the collateral in its present condition or following any commercially reasonable preparation or processing.

2/ The secured creditor may select the method, manner, time, place and other aspects of the sale or other disposition lease or license, including whether to sell or otherwise dispose of, lease or license collaterals individually, in groups or as a whole.

3/ The secured creditor may transfer the ownership of the collateral to the buyer at a public auction or if no buyer appears at the second auction, to acquire the property at the floor price set for the first auction and have the ownership of the property transferred to it.

ሀ) መያዣውን መልሶ ለመውሰድ፣ ለመያዝ፣ ለማስተላለፍ ዝግጁ ለማድረግ፣ ለማሻሻል እና ለማስተላለፍ ለሚወጣ ተገቢ ወጪ፣

ለ) መያዣውን ለማስተላለፉ መነሻ በሆነው የዋስትና መብት ላይ ያሉ ግዴታዎችን ለመወጣት፣እና

ሐ) የገቢው ክፍፍል ከመጠናቀቁ በፊት የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ድርሻው እንዲሰጠውና ዋስትና የተገባላቸው ግዴታዎች እንዲፈጸሙ ጥያቄ ከቀረበ፣

በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ቅደም ተከተል መሠረት ክፍያውን ይፈጽማል፡፡

፪/ የበታች የሆነ የዋስትና መብት ወይም ሌላ ዋስትና ያለው ሰው ስለጥቅሙ ወይም ስለዋስትና መብቱ ሌላ ዋስትና ባለው ገንዘብ ጠያቂ ከተጠየቀ ተገቢውን ማረጋገጫ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልተፈፀመ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት የበታች የሆነ የዋስትና ባለመብቱ የሚያቀርብለትን ጥያቄ ለማክበር አይገደድም፡፡

፫/ በተወዳዳሪ ባለመብቶች መካከል የመብት ወይም የቀዳሚነት ክርክር ሲነሳ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የፍርድ ቤት ወይም ሌላ ሥልጣን ያለው አካል ትዕዛዝን የያዘ ባለመብት እስከሚመጣ ድረስ ትርፉውን ገንዘብ ወለድ በሚያስገኝ ዝግ ሂሳብ ውስጥ እስከ ስልሳ ቀናት ለማስቀመጥና ሂሳቡንም ይዞ ለማቆየት ይችላል፡፡

፬/ የዋስትና መብት በማስከበር የሚገኘው ገቢ ዋስትናው የተጠበቀ ግዴታን ለመወጣት ከዋለ በኋላ ላልተከፈለው ቀሪ ዕዳ ባለዕዳው ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

a) the reasonable expense of retaking, holding, preparing for disposition, processing and disposing of the collateral;

b) the satisfaction of obligations secured by the security right under which the disposition is made; and

c) the satisfaction of obligations secured by any subordinate security right or other subordinate lien in the collateral if the secured creditor receives from the holder of the subordinate security right or other lien a demand for proceeds before distribution of the proceed is completed.

2/ If requested by the secured creditor, a holder of a subordinate security right or other lien shall furnish reasonable proof of the interest or lien within a reasonable time. Unless the holder does so, the secured creditor need not comply with the holder's demand under Sub Article (1) (c) of this Article.

3/ Where there is a dispute as to the entitlement or priority of any competing claimant, the enforcing secured creditor may deposit the surplus in an interest bearing blocked account within sixty days and keep the account until a claimant comes up with an order of court or any competing organ.

4/ A debtor remains liable for any shortfall owing after application of the proceeds of enforcement to the secured obligation.

**፹፮. በመያዣው ላይ ስለሚገኝ መብት**

፩/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው ከሺያጩ ወይም ከአስተላላፊው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር መያዣውን የማስያዝ መብት የሚያገኘው መያዣውን ከሸጠውና የበታች የሆነ ተወዳዳሪ የዋስትና መብት ነጻ በሆነ መንገድ ነው፡፡

፪/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ መያዣውን ካከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ፣ ተከራዩ ወይም ፈቃዱ የተሰጠው ሌላ ቀዳሚ የዋስትና መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከሌለ በስተቀር ኪራዩ ወይም ፈቃዱ በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የሚያስገኘውን ጥቅም ያገኛል፡፡

፫/ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ውጭ መያዣውን ከሸጠ ወይም ካስተላለፈ፣ ካከራየ ወይም የመጠቀም ፈቃድ ከሰጠ ገዢው ወይም የተላለፈለት ሰው፣ ተከራዩ ወይም ባለፈቃዱ በመያዣው ላይ መብት ወይም ተጠቃሚነትን የሚያገኘው ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች በመጣስ መያዣ ሰጪውን ወይም የሌላን ሰው መብት ጉልህ በሆነ አኳኋን መጉዳቱን ካላወቀ ነው፡፡

**፹፯. ከተሰብሳቢ ሂሳብ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነድ፣ በተቀማጭ ሂሳብ ገቢ ከተደረገ ገንዘብ ወይም ከሴኩሪቲ ክፍያ ስለመሰብሰብ እና ስለመጠየቅ መብት**

፩/ ከግዴታ አለመወጣት በኋላ በተሰብሳቢ ሂሳብ፣ በተላላፊ የገንዘብ ሰነድ ወይም ሴኩሪቲ ላይ ዋስትና ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከተሰብሳቢው ሂሳብ ባለዕዳ፣ ከተላላፊ የገንዘብ ሰነዱ ተገዳጅ ወይም ከሴኩሪቲ አውጪው ክፍያ መሰብሰብ ይችላል፡፡

**86. Rights Acquired in Collateral**

1/ If a secured creditor sells or otherwise disposes of the collateral, a buyer or other transferee acquires the grantor's right in the asset free of the rights of the enforcing secured creditor and any subordinate competing claimant, except the right that have priority over the security right of the enforcing secured creditor.

2/ If a secured creditor leases or licenses the collateral, a lessee or licensee is entitled to the benefit of the lease or license during its term, except as against creditors with right that have priority over the right of the enforcing secured creditor.

3/ If a secured creditor sells or otherwise disposes of leases or licenses the collateral not in accordance with the provisions of this Part, a buyer or other transferee, lessee, or licensee of the collateral acquires the right or benefit, provided that it had no knowledge of a violation of the provisions of this Part that materially prejudiced the right of the grantor or another person.

**87. Collection of Payment Under a Receivable, Negotiable Instrument, Right to Payment of Funds Credited to a Deposit Account or Security**

1/ After default, a secured creditor with a security right in a receivable, negotiable instrument, or security is entitled to collect payment from the debtor of the receivable, obligor under the negotiable instrument, or issuer of the security.

**፺፮. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን የ፲፪ ወራት ማለቅ ወይም የመያዣ መዝገቡ ሥራ መጀመር ከሁለቱ በቀደመው በአንደኛው ቀን የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**96. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force on the date of the expiry of 12 months after publication in the Negarit Gazette or the commencement of operation of the Collateral Registry, whichever comes first.

Done at Addis Ababa, this 7th day of August, 2019

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERALDEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**